ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት

ዙር ሠላሳ



#የዲጂ ጥግ

ሀሐም ኧውን ይሆናል!

#ታሳሣሥ
በኢትዮጵያ ትልቁ ሁነት
ሀበሻ ገና እና ፋሲካ ኤክስፖ

#አዲስ
ቸሊና
በአዲስ አልበም

#ሀገርኛ
ሜዳ ቻት
በሃገር ቋንቋ፣ የሃገር ልጅ ሥራ

በዚህ እትማችን

ጥር ወር፣ 2011 ዓ.ም.



9 - 13
#የዲጄ ጥግ
ህልም እውን ይሆናል

7 - 8
#ታሳሣሥ
በኢትዮጵያ ትልቁ ሁነት
ሀበሻ ገና እና ፋሲካ ኤክስፖ

4 - 6
#አዲስ
ቸሊና
በአዲስ አልበም









17 - 19 **#ዓለም** THE TONIGHT SHOW | 13 **#ሀገርኛ** ሜዳ ቻት በሃገር ቋንቋ፣ የሃገር ልጅ ሥራ

ዙር ሠላሳ
በዳሰሳ አዲስ ጎትመትና ማስታወቂያ ኃላ. የተ. የግል ማኅበር የምትዘጋጅ ወርሃዊ ዲጂታል መጽሔት ናት።
ጎዳር፣ 2011 ዓ.ም ተመሰረተ

ያግኙን
+251 924 312 097
addisaccess@gmail.com
ጉርድ ሾላ፣ ጂ እና ቢ ህንጻ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 310

በመስመር ላይ (Online)
@AccessAddis
@AccessAddis

የግራፊክስ ዲዛይን ማሰራት ይፈልጋሉ?

ቤል ግራፊክስና ፎቶግራፊ

+251 910 137 350



የዋና አዘጋጁ መልዕክት

ጤና ይስጥልኝ! መዝናኛ ማለት የሰውን አእምሮ የሚያፍታታ ከመደበኛ የኑሮ ጫንቀቶችና ሃሳቦች የሚያላቅቅ እና የሚያሳርፍ ነው። ይህ ደግሞ ለእያንዳንዱ ሰው ቢለያይም አላማው ግን ማዝናናት ነውና ሁሉም መንገዶች የራሳቸው የጋራ እሴቶች አሏቸው። እኛ የዙር ሰላሳ ቤተሰቦች በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ ስንገኝ ግን በተለይ በተለይ ስነ ምግባርን በጠበቀ መልኩ ማዝናናት እና መዝናናት ላይ ያሉ ችግሮችን እናስተውላለን። መዝናናት ማለት በሱሶች መያዝ፣ መጣላት እና መስከር ማለት አይደለም፤ ማዝናናት ማለትም እነዚህኑ ችግሮች ማበረታታት፣ ታዳሚውን አለማክበርም መሆን የለበትም።

ለዚህ ደግሞ ሁሉም ለየራሱ ኃላፊነት የሚወስድ ቢሆን ያሉት ችግሮች ሁሉ ሊቀረፉ የሚችሉ እንደሆኑ እናምናለን። ዙር ሰላሳም መዝናኛውን ስታበረታታ ማንነትና ራስንና ሌሎችንም በሚያከብር መልኩ እንዲሆን እየመከረች የዚህን ወር እትማችንን ስናደርሳችሁ እናንተም እንደምትደሰቱበት በማመንና አብራችሁን እንድትዘልቁ በመጋበዝ ይሆናል።

ቆይ ቆይ አንዴ! በዚህ እትማችን ላይ ጥያቄዎችን የያዘች አንድ አምድ ጨምረናል። ባስቀመጥነው የመመለሻ መንገድ መሠረት ቀድመው ለመለሱ ሶስት አንባቢዎቻችን በየጊዜው ከምንሰጣቸው ነፃ የዝግጅቶች መግቢያ ካርዶች ውስጥ የአንዱ ዝግጅት የቅድሚያ አሸናፊ ይሆናሉ። መልካም ንባብ!!

ዋና አዘጋጅ
ፍጹም ዓለማየሁ
fiseha.tsion1@gmail.com

የገበያ ዳይሬክተር
ቴዎድሮስ ብርሃኑ
tediberhani@gmail.com

አዘጋጅ
ኢሳያስ ሽፈራው
esoabi29@gmail.com

የሽፋን ፎቶግራፍ
በዳሰሳ አዲስ

ቶሊና

አዲስ አልበም





ፎቶ: ቪንቴጅ ፒክስል ፎቶግራፋ

#አዲስ

#አዲስ

ውልደቷ በውቢቷ ከተማ ሐዋስ ከተማ እድገቷ በአዲስ አበባ የሆንው ድምጻዊት የመጀመሪያ ስራዋን ከ 7 ዓመት በፊት መድረክ ላይ እንድትቅርብ እድሉን የሰጣት አንጋፋው የኤክስፕረስ ባንድ ሲሆን ከዛ በማስቀጠል ማማስ ኪችን፣ጃዝ አምባ፣ሽራተን አዲስ ከተለያዩ ባንዶች ጋር በመሆን የተልያዩ የድምፃዊያን ስራዎች በማቅረብ በተለይም የባህር ማዶ ድምፃውያን ስራዎች በመጫወት ትታወቃለችም ከ3 ዓመት በፊት "ሳይ ባይ " የተሰኘ የመጀምሪያ ስራዋን ህዝብ ዘንድ አቅርባለች ከዚህ በመቀጠልም "ዜማዬ" የተሰኘውን ሰራዋን ለህዝብ አድርሳለች። ከኪነ-ጥበብ ባለሙያ ቤተሰቦች የተገኘችው ድምፃዊቷ የትግርኛ ሙዚቃ አቀንቃኝ የሆነችው እናቷ ለታይ መስፍን ብዙ የሙዚቃ ስራዎችን ስታቅርብ ከመድርክ ጅርባ በመሆን ስትከታተል ማደጓ ወድ እዚህ ሙያ



ፎቶ: ቪንቴጅ ቺክስ ፎቶግራፊ

#አዲስ

እንድትገባ ትልቁን አስትዋፅዎ እንዳደርገላት ትናገራለች። ይህች ድምፃዊት በሙሉ ሰሟ ቸሊና ይሺወንድም ስትባል በቅርቡ በራሷ ስም መጠሪያ የሰጠችውን የመጀመሪያ አዲስ አልበም ለሙዚቃ አፍቃሪያን አቅርባለች። ከ 2 ዓመት በፊት አልቆ በተለያዩ ምክንያቶች ለህዝብ ዘንድ ሳይደርስ የቀርው አልበም ባሳለፍንው ውር የሙዚቃ ገበያውን ተቀላቅሏል። በዚህ አልበም ላይም የተለያዩ የሃገራችን የሙዚቃ ባልሙያዎች እንድ ያሙሉ ሞላ፣ጀርጋ መስፍን ፣ ዘሩባቤል ሞላ፣ኪሩቤል ተስፋዬ፣እሱባልው ይታይው እና ሌሎችም በትለያዩ ዘርፉች በመሳትፍ የየራሳቸውን እሻራ በዚህ አልበም ላይ አስፍረዋል። ውድ የዙር ሰላሳ ዲጅታል መፅሔት ተከታታዬች የዚህን አልበም ሲዲ ኦርጂናሉን በመግዛት እየተዝናናችሁ ኪነ ጥበብ እኛ ከምንያኑን ያግዙ ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን።



ፎቶ. ቮጋዥ ፒክስል ፎቶግራፊ



በኢትዮጵያ ትልቁ ሁነት

ሀበሻ ገና እና ፋሲካ ኤክስፖ



ፎቶ፡ ከሐበሻ ዊክሊ



ፎቶ: ከሐበሻ ዊክሊ

ሀበሻ ገና ኤክስፓ ባሳለፍነው ታኅሳስ ወር የገናን በዓል ምክንያት በማድረግ በሃበሻ ዊክሊ ፕሮሞሽን አዘጋጅነት በኤግዝብሽን መዓከል ለ23 ቀናት ዝግጅቱን በማካሄድ ከ500 በላይ ተሳታፊ ድርጅቶች ምርት እና አገልግሎታቸውን 500ሺ በላይ ለሆኑት ጎብኝዎች በማቅረብ ግብይቶች ሸመታዎችን በማድረግ አሳልፈዋል። ከግብይቱ እና ሸመታው ባለፈ ለጎብኝዎች የገና በዓልን በማይረሳ እና አስደሳች በሆነ ሁኔታ እንዲያሳለፉ እድሉን አመቻችታል። በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነውን የዳይኖሰር ትዕይት፣ ለተከታታይ 23 ቀናት ከ100 በላይ አንጋፋ እና ወጣት ሙዚቀኞችን በመጋበዝ የሙዚቃ ዝግጅቶችን አከውኗል ሃበሻ ዊክሊ ፕሮሞሽን በ65 ሚሊዮን ብር በላይ በጀት በመበጀት ለሁለቱን በዓላት ማለትም ያለፈውን ገና እና መጪውን ፋሲካ ኤክስፓ በማዘጋጀት ለአዲስ አበባ እና ለአካባቢዋ ነዋሪዎች የመዝናኛ እና የመገበያያ አማረጮች በማቅረብ የመጀመሪያውን የገናውን ኤክስፓ በተሳካ ሁኔታ በማዘጋጀት የገና ዋዜማ ለእለት ተወዳጁን ድምፃዊ ሳሚ ዳን የመዝጊያ ዝግጅቱን በማድመቅ ለመጪው ፋሲካ ከዚህ ቀደሙ በተለየ እና በተሻለ መንገድ በአዳዲስ ትዕይንቶች እንደሚመጡ ታዳሚውን ቀጠሮ አስይዟል።








RECORDS

ሀልም እውን ይሆናል!


#የዲጄ
ጥግ


Pioneer Dj
rekordbox
DDJ-RZX
PROFESSIONAL DJ CONTROLLER
rekordbox
Pioneer Dj



ቅን ልቦና፣ የነቃ ህሊና፣ በጎ አእምሮ.... እነዚህን አጣምሮ የያዘ ሰው ሁሉ ይመኛል። ምኞቱ ሁሉ ማቆሚያ የለውም። አንድ እርምጃ የተራመደው ሁለተኛውን ለመጨመር ባለሁለትኛውም ቀጣዩን... ይህ ምኞት ሲያድግና ሲጎለምስ ምኞቱ ላይ ለመድረስ ብቻ ሳይሆን እንዴት እንደሚደርስ በአስተውሎ ማቀድ ሲጀመር ደግሞ ምኞቱ ሕልም ይሆናል። በቀን የሚታሰብ በሌሊት የሚታይ፣ በልቦና የሚዳሰስ፣ ገዘፍ አካል ነስቶ እስክያዩት የሚያጓጓ እየሆነ ይሄዳል። ሕልም ያለው ሰው የሚያስበውን ያውቃል, የሚፈልገውን ከመረዳት አልፎ ማስረዳት ይችላል፣ ሕልሙን እውን ያደርገዋል ሲጀምር ከጉዞው የሚገታው አይኖርም።

የዙርሰላሳ ዝግጅት ክፍል ባልደረቦች በዲሲቲ ኢንተርቴይመንት ግቢ ስንገኝ የምህፃረ ቃሉን ፍቺ ለመረዳት ብዙ ብንገምትም በኋላ ከሰማነው ትርጉም ግን ጫፉ ላይ እንኪን አልደረስንም ነበር። የድርጅቱ መስራችና ባለቤት አቶ ሙራድ ጋር ተዋውቀን በትህትና ለመጎብኘት ከወሰድን በኋላ ግን በጭውውታችን መጀመሪያ DCT ማለት (Dream Come True) መሆኑን ተረዳን። ሕልም ይዞ የተነሳው ድርጅት መስራች እውን ያደረገውን ሕልሙን ሲሰይመው ሕልም እውን እንደሚሆን ተናገረበት።

ዲሲቲ ኢንተርቴይመንት በሀገራችን የመዝናኛ ዘርፍ ላይ ያለውን ችግር ተመልክቶ አራት ዘርፎችን በአንድ ጥላ ስር ያቀፈ ተቋአም ነው ። በግቢው ውስጥ በተመለከትናችው ክፍሎች ውስጥ ሙሉ የሪከርድ ስቱዲዮ የዘመኑን የመጨረሻ





ጥራት ደረጃ የጠበቁ መሳሪያዎችን አካትቶ የያዘ የድምፅ ክፍል ሲሆን ሬድ ካሜራዎችን፣ ድሮኖችን እንዲሁም ዘመናዊ ኮምፒዩተሮችን ያሉበት የቪዲዮ ክፍል እንዲሁም የሁነቶች አስተባባሪነት ስራዎችን እንድሚሰራ ተረድተናል። በአራተኛነት ግን ቀድሞም አቅደን የሄድንበት ለየት ያለ ክፍል ነበር, የሙዚቃ ትምህር ቤቱ፣ ይህ ትምህርት ቤት ከለመድናቸው የሙዚቃ መሳሪያዎች በተጨማሪ የዲጄነት ትምህርትን በሰፊው ለመስጠት ዝግጅቱን አጠናቁአቋል። በክለቦች፣ በኮንሰርቶች፣ በሰርጎችና ሌሎችም ዝግጅቶች ላይ ዲጄ መጥራትና ማዝናናት በጣም እየተለመደ የመጣ ቢሆንም እንኳን የሀገራችን ዲጄዎች ግን ከልምድ እና ከግል ጥረት ከሚገኝ እውቀትና ችሎታ ባለፈ በትምህርት የተደገፈ ሙያ ያላቸው የሉም፣ ቢኖሩም በጣት ሊቆጥሩ የሚችሉ ናቸው። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ያለመው ይህ ተቋአም በዓይነቱ አዲስ የሆነውን ይህንን ትምህርት ቤት ሲከፍት የፓዮኒር ብራንድ የሆኑ የዲጄ መሳሪያዎችን SP3 ከሚባለው በሀገራችን ያሉ በርካታ ዲጂዎች

ከሚጠቀሙበት ነገር ግን ለትምህርት ቤቱ ትንሹ ከሆነው ጀምሮ እንደ ዲጄ ካሊድ ያሉ የዓለማችን እጅግ ስመ ገናና ዲጄዎች የሚጠቀሙበት DDJRZX ሞዴል ድረስ ሁሉንም መሳሪያዎች ከማክ ኮምፒዩተሮች ጋር አጣምዶ ይዟል።

ትምህርት ቤቱ በሶስት ደረጃዎች የዲጄነት ትምህርትን ለመስጠት ሲያቅድ፣ በመጀመሪያ ምንም አይነት እውቀትም ሆነ ከመሳሪያዎቹ ጋር ትውውቅ ለልላቸው ሰልጣኞች የጀማሪነትን፣ በመጡኑ የሚያውቁና በዲጄነት ለተወሰነ ጊዜ የቆዩትን በመካከለኛነት እንዲሁም በሀገራችን ለረጅም ዓመታት በዚሁ ሥራ ላይ የቆዩ ነገር ግን ራሳቸውንና ስራቸውን በስልጠናና በዓለም አቀፋዊ እውቀት መደገፍ ለሚፈልጉ ድጄዎች ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የስልጠና መርሃ ገብር አዘጋጅቷል። በተለይም ደግሞ ከአቶ ሙራድ እንደተረዳነው የኢትዮጵያ ዲጄዎች ማኅበር እና አመራሮች ይህንን ጉዞ ከመደገፍ ባለፈ ራሳቸውም ስልጠናውን ለመከታተል ያሳዩትን ፍላጎት ከልብ አድንቀናል።

የዲሲቲ የዲጄዎች ማሰልጠኛ መሳሪያዎችን በመጠቀም ላይ ብቻ ያተኮረም እንዳይመስላችሁ። እንደሚታወቀው ዲጂዎች በሚሰሩባቸው ክለቦችም ይሁን ማንኛውም መድረኮች የሚገኙ ታዳሚዎች የተለያየ የኋላ ታሪክ፣ ማንነት እና ስሜት ይዘው የሚገኙ ናቸው። ታዲያ እንደ አዝናኝ ዲጄው በሙዚቃ አመራረጡም ሆነ በመድረክ አቀራረቡ እነዚህን ሰዎች ማስደሰት የሚጠበቅ ነው። ለዚህ ደግሞ የስነ ምግባርና የሳይኮሎጂ ንፃሬን ጨምሮ እንደሚሰጥ አውቀናል።

በዚህ ትምህርት ቤት ዲጄነትን ለመማር ሲመጡ ደግሞ ዘርዘር ያለ የሙዚቃ አውቀትን ከማቀናበር ችሎታ ጋር እንዲያዋህዱ የሚረዳ ትምህርትም አለ። አቶ ሙራድ "...ዓለም ላይ ያሉ ትልልቅ አቀናባሪዎች ዲጄዎች ናቸው ምክንያቱም ህዝቡ ምን አይነት ሙዚቃ እንደሚፈልግ በመካከል ድልድይ ሆነው ያሉት ዲጄዎች ናቸው" ሲሉ ሙዚቃ የማቀናበር ችሎታ ያለው ዲጄ ሕዝቡን ማስደሰት የሚችል ሙዚቃ መስራት እንደሚችል ያብራራሉ።

ይህንን ትምህርት ቤት በሀገራችን ለማቋቋም መስራቹ ብዙ ቦታዎችን ረግጠዋል የትምህርት አሰጣጡን ለመረዳት ሲልም መምህር ማግኘት በራሱ ፈተና ነበርና ከአሜሪካ, አትላንታ, በቅርባችን ከሚገኙት ሃገራት ደግሞ ኬንያ, ኡጋንዳ እና ታንዛኒያ ሄደው ከተመልከቱት ልምድ ዘመኑን የሚመጥኑ መስርያዎችን ያሟሉ ሲሆን ስልጠናውን ለመስጠት ደግሞ የረጅም ዓመታት ዲጄዎችን የማስተማር ልምድ ያለውን ዲጄ ሬቭ ከኬንያ አምትተውታል።

ስልጠናው ከስድስት ወር እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ጊዜ እንዲጠናቀቅ ተደርጎ የተቀረፀ ሲሆን ለጀማሪዎች ምንም አይነት ቅድመ አውቀት አይጠይቅም። ይህ



ስልጠና ካለው ወጭና የትምህርት ቤቱ የጥራት ደረጃ አንፃር ትልቅ የሚባል ቢሆንም ሰልጣኞችን ለማበረታታት ሲባል ሊያስጠይቅ ከሚችለው ክፍያ ላይ ሰባ በመቶ ቅናሽ በማድረግ ምዝገባውን እያካሄደ ይገኛል።

ሕልሙ ግን አላበቃም ዲሲቲ "ዲጄ ፌስት" ማዘገጀት ይፈልጋል, በምስራቅ አፍሪካ የሚገኙ ዲጄዎች ሁሉ የሚሳተፉበት። በምስራቅ አፍሪካ በሚገኙ ሃገራት በየጊዜው ለማዘጋጀት በታቀደው በዚህ ፕሮግራም ላይ ከትምህርት ቤቱ የወጡ ዲጄዎች ሌሎች የስራ እድሎችን የማግኘት እና በሌላ ሀገር ታዳሚዎችም ፊት የመስራት አጋጣሚን ያገኙበታል። ደግሞም ጥሩ ውጤት ያላቸው ሰልጣኞች በዲሲቲ ኢንተርቴይመንት ውስጥ የመስራት ዕድል የሚያገኙ ሲሆን ከተለያዩ ታዋቂ ከለቦች ጋር በመነጋጋርም ሰልጣኞቹ የተግባር ልምምድ ማድረግ የሚሉበት መንገድ የተመቻቸ ነው።

dct ENTERTAINMENT






ምርትና አገልግሎትዎን በዳሰሳ አዲስ የማህበራዊ ገጾችና በዙር ሠላሳ ላይ ያስተዋውቁ።

500,000

ሰዎች ያዩዎታል


ዳሰሳ አዲስ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃላ. የተ. የግል ማኅበር
+251 924 312 097
addisaccess@gmail.com
ጉርድ ሾላ፣ ጂ እና ቢ ህንጻ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 310



በሃገር ቋንቋ፣ የሃገር ልጅ ሥራ

የዛሬ አስር ዓመት ገደማ ትንንሽ ስልኮችን በይክሳችን ይዘን ስንዞር እና ስናወራ፣ ስክሪናቸው የሚነኩ ስማርት ስልኮችን ሳንይዝ በፊት ሁለት ሜጋ ፒክስል ጥራት ያላቸው ሞባይል ስልኮች እንኳን ብርቅ በነበሩበት ጊዜ ምስሎችንና ዶክመንቶችን ከስልክ ላይ መላላክ እንዲሁም አጠገብ እንዳለ ሰው ቻት ማድረግ በዓለም ዙሪያ ካሉ ሰዎች ጋር ሁሉ በIM (Internet Messaging) እንደዚህ መቀራረብ እንደሚቻል የሚነግረን ሰው ቢኖር ለብዙዎች ለማመን ከባድ በሆነ ነበር::

ዓመታት በዓመታት ሲተኩና ቴክኖሎጂውም ከዘመናት ፍሰት ሁሉ በላቀ ፍሰት ሲመጥቅ ግን ትሩፋቶቹ ለኛም ተርፈው በቅድሚያ የሞባይል ኢንተርኔትን ከመጠቀም የጀመረው እድገት በተለይም የስማርት ስልኮች በከፍተኛ ሁኔታ ዋጋ መቀነሳቸውን እንዲሁም ትልልቅ የሞባይል አምራች ኩባንያዎች የአፍሪካን ገበያ አላማ አድርገው መንቀሳቀሳቸው በተጨማሪ ደግሞ Open Source የሆነው የአንድሮይድ መፈጠር የተጠቃሚዎችን ቁጥር በእጅጉ ሲጨምር አጠቃቀሙም እያደገ እንዲቀጥል አስችሎታል::



ቫይበር፣ ዋትስ አፕ፣ የፌስ ቡክ ሜሴንጀር፣ ጉግል ቶክ (አሁን ሀንግ አውት)፣ ኢሞ፣ ቴሌግራም በየራሳቸው የመጠቀሚያ መንገዶች በየወቅቱ ስንጠቀማቸው ቆይተናል። አሁን ግን የሀገራችን ልጆች የራሳችንን ቋንቋዎች እና ለኢትዮጵያውያን በተዘጋጁ አቀራረቦች ሜዳ ቻት የተሰኘ መተግበሪያ አቅርበውልናል። የሜዳ ቻት መስራችና ሥራ አስኪያጅ የሆነውን ብሩክ ታይሉን ስለመተግበርያው ጠይቀን እናም ያወቅነውን እንደዚህ ይዘን መጥተናል።

ሜዳ ቻት ለእኛ ሀገር ተጠቃሚ ታስቦ የተሰራ እንደመሆኑ መጠን ሌሎቹ የመልክት መላላኪያ መተግበሪያዎች ከሚሰጧቸው አገልግሎቶች ለየት ባለ መልኩ ሶስት የሀገራችንን ቋንቋዎች ያካተተ ሲሆን በተለይ ደግሞ ከአሞሌ የሞባይል ክፍያ ስርዓት ጋር በመቀናጀት ብር ለመላላክ፣ የሞባይል ካርድ እና ሙዚቃዎች ለመግዛት እና ሌሎችንም እንደ ክፍያዎች ለመፈፀም እንዲያስችል ተደርጎ ተሰርቷል።

መተግበርያው በተለይም ደግሞ አሁን አሁን እጅግ አሳሳቢ የሆነውን የመረጃ መረብ ደህንነት መስተጓጎል ችግር እንዳያጋጥመው የሚላኩ መልዕክቶችን ከላኪውና ከተቀባዩ ሁለት ፅንፎች በሚኖሩ የተለያዩ የምስጢር ቁልፎች እንዲናበቡና በየትኛውም መካከል በሚገኝ ሰርቨር ላይ መከፈት እንዳይችል ተደርጎ የሚቆለፍ መሆኑ የታመነ እንዲሆን ያስችለዋል። በተጨማሪም ስልክዎ ቢጠፋ ወይም ስልክ ቢቀይሩ መተግበሪያውን ድጋሚ በመጫንና ወደ መለያ አድራሻዎ ብቻ ሲገቡ መልዕክቶችዎ ሁሉ እንደነበሩ ስለሚያገኙአቸው የሚያሳስብዎ ነገር አይኖርም።


ሜዳ በአሁኑ ሰዓት ከአስራ አራት ሺህ በላይ ተጠቃሚዎችና ያፈራ ሲሆን በተለይ ደግሞ የመተግበርያው ተጠቃሚ ከሆኑ በሜዳ ጌም ላይ በመሳተፍና በቀጥታ የጠቅላላ እውቀት ጥያቄዎችን በመመለስ እስከ 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ድረስ ማሸነፍ ይችላሉ።

ዙር ሰላሳ ኢትዮጵያዊ ነች። ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያ የሆኑትን ሁሉ ታከብራለች። ለዚያም እሴቶቻችንን፣ ፈጠራዎቻችንንና የእኛ የሆኑትን በ **#ሐገርኛ** ትዘክራለች።

የአንድሮይድ ተጠቃሚ ከሆኑ የሜዳ ቻት መተግበሪያን [እዚህ ያውርዱ።](#) ወይም ኮዱን ይጠቀሙ።










THE TONIGHT SHOW

“The Tonight Show” የሚለው ስያሜ በአሜሪካን ሀገር ከስልሳ ዓመታት በላይ ይታወቃል:: በቴሌቪዥን ታሪክ ውስጥ ባለሙሉ ቀለም ስርጭት እንኩአን ሳይጀመር እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ከ1954 ጀምሮ እስከ 1960 ድረስ በጥቁር እና ነጭ ቀለማት በመተላለፍ የተጀመረው የዓለማችን ረዥሙ የውይይት ትዕይንት (Talk Show) ባለቀለም ምስልንና 480i የምስል ጥራትን በታሪኩ መዝግቦ ዘመኑ የደረሰበትን HDTV 1080i የምስል ጥራት ጠቅልሎ በየቀኑ ለNBC የኔትዎርክ ቴሌቪዥን ተመልካቾች መቅረቡን ቀጥሏል::



ይህ ዝግጅት ከአስራ ሁለት ሺህ በላይ ዝግጅቶች የቀረቡበት ከመሆኑ በላይ አሁን ከሚጠራበት “The Tonight Show Starring Jimmy Fallon” ከሚለው መጠሪያ በተወሰነ መልኩ የሚለዩ, የአቅራብዎችን ስም የሚያካትቱ ስያሜዎችን በመያዝ ሲታይ የቆየ ሲሆን እስካሁን ድረስ የአሁኑን አቅራቢ (Host) ጂሚ ፋለንን ጨምሮ ስድስት የተለያዩ ኮሜዲያን ተፈራርቀውበታል::

ጃንዋሪ 25 ቀን 1957 አንድ ተብሎ በስትቭ አለን አቅራቢነት የተጀመረው ይህ ፕሮግራም ጃክ ፓር, ጆኒ ካርሰን, ጄይ ሌኖ እና ኮናን ኦ’ብራያን ከዚህ

ቀደም በአቅራቢነት ቆይተውበታል:: በተለይ ደግሞ ጆኒ ካርሰን ሰላሳ ምዕራፎችን (Seasons) ወይም 4,531 ዝጅግቶችን በማቅረቡ የረጅም ጊዜ አቅራቢነት ክብረ ወሰኑን የያዘ ሲሆን በሥስተኝነትና መልሶ ደግሞ በአምስተኝነት የፕሮግራሙ አቅራቢ የነበረው ጄይ ሌኖ ከቴልቪዥን ኔትዎርኩ ጋር የነበረው አስገራሚ ግንኙነትና ለስላሳነት በከፍተኛ ሁኔታ መነጋገሪያና የሌሎችም የምሽት ትዕይንቶች መሳለቂያ አድርጎት ነበር::

“War of the Late Night Shows” እየተባለ በብዛት የሚነሳው ይህ አጋጣሚ የተፈጠረው ጄይ ሌኖ ከአምስት ዓመታት በኋላ ፕሮግራሙን ለኮናን ኦ’ብራያን እንደሚያስረክብ ይነገረዋል; ነገር ግን በዚያን ወቅት ከኔትዎርኩ ጋር ያለው ውል የማይጠናቀቅ በመሆኑ እዚያው ቴሌቪዥን ላይ ሌላ ዝግጅት እንዲያቀርብ ሲታዘዝ ያለተቀውሞ መቀበሉ በራሱ ዝግጅት ላይ ጭምር በቀረቡ ሰዎች እንዲሾፍበት ያደረገው ሲሆን ሌላኛው ፕሮግራሙም በተደጋጋሚ የሰዓት ለውጥ ሲደረግበት ይባስ ብሎም በርካታ ሰው ቴሌቪዥን ከሚከታተልበት ሰዓት (Prime Time) ተገፍቶ ሲወጣ አለማንገራገሩ ትልቅ ውርደትን ፈጥሮበታል:: ይህ የቴሌቪዥን ኔትዎርክ ይህንኑ ሰዓት የማሸጋሸግ ሙከራ ኮናን ኦ’ብራያን ላይ መሞከሩ አለመስማማትን እንዲሁም ከአንድ መቶ አርባ ስድስት ዝግጅቶች በሁአላ ውሉ ሳይጠናቀቅ አቅራብነቱን እንዲያቋርጥና እስካሁን ካሉት አቅራቢዎች ለአጭር ጊዜ የቆየው እንዲሆን ቢያደርገውም ጄይ ሌኖ ግን ኮናን የተወውን ዝግጅት መልሶ ለመቀበል መስማማቱ የአንድ ወቅት መነጋገሪያ ሆኖ ነበር::

#ዓለም

ፌብሩዋሪ 6 ቀን 2014 የመጨረሻው ጄይ ዝግጅት ከቀረበ በኋላ ዝግጅቱን ወጣቱ ኮሜዲያን ጂሚ ፋለን ተረክበት ቀጥሏል:: እስካሁን ድረስ ከአንድ ሺህ በላይ ዝግጅቶችን ያቀርበው ጂሚ ፋለን የዝግጀቱን የቀረፃ ቦታ ከአርባ ሁለት ዓመታት በሁአላ ከሰሜን ካሊፎርኒያ ወደ ኒውዮርክ እንዲመለስ ቀረፃው የሚካሄድበት ስቱዲዮ 6Bም በአምስት ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር እንዲታደስ ከማድረጉ በተጨማሪ የራሱን የአቀራረብ ዘዴ በመጨመር ዝግጅቱን ከፍ ማድረግና እንደ “Lip Sync Battle” ያሉ ዝግጅቶች ከእርሱ የዝግጅት አካልነት እንዲወጡና ራሳቸውን የቻሉ ዝግጅቶች መሆን እንዲችሉ አድርጓል::

ዝግጅቱ በአሁኑ ወቅት “The Roots” የተሰኘውን ባንድ የቤቱ ባንድ አድርጎ የያዘ ሲሆን ከምሽቱ 5:15 ጀምሮ ይተላለፋል”::
የተለያዩ የዝግጅት ክፍሎች ያሉት ይህ ዝግጅት ጂሚ ፋለን ከዚያ ቀደም ያቀርበው ከነበረው



#ዓለም

ፕሮግራም ላይ በመዋስ ብዙዎቹን ያካተተበት ሲሆን Pros & Cons, Tonight show Hashtags, Thank you Notes, Ew!, Do not Read List እና Screen Grabs የተሰኙት ክፍሎች በተደጋጋሚ የሚቀርቡና የተወደዱ ክፍሎች ናቸው:: ይህም ሲባል የውይይት ትዕይንት እንደመሆኑ መጠን የሚቀርቡት እንግዶች ሳይዘነጉ ማለት ነው::

በእንግዶች አቀራረብም ቢሆን ከታዋቂ ዘፋኞችና ተዋንያን ጀምሮ በፖለቲካው ዓለም በምድረ አሜሪካ ትልልቅ የሆኑት የቀድሞው ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማና የአሁኑ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ የቀረቡ ሲሆን በተለይ ባራክ ኦባማ በስልጣናቸው ዘመን ለተማሪዎች ትምህርት ወጪ የሚሰጥ ብድር ላይ የሚደረግ የዕዳ ጭማሪን ተቃውመው ኮንግረሱን ለማሳመን የህዝብ ድጋፍ ለማሰባሰብ ከጂሚ ፋለን ጋር በሙዚቃ ጭምር ያደረጉት ቅስቀሳና የአሁኑ ፕሬዚዳንት ሚስተር ትራምፕ ስልጣኑን ከመረከባቸው በፊት የፀጉራቸውን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ በጂሚ እጅ ሲመሰቃቀል ማየት አስገራሚም አስቂኝም አጋጣሚዎችን የፈጠረ ነበር::

ምንም እንኳን ይህንን ዝግጅት እኛ ሀገር ላይ በቀጥታ ለማየት ባይቻልም በዩ ትዩብ ላይ ይፋዊ ቻናሉን በመከታተል ወይም በNBC መካነድር ላይ በመግባት ዝግጅቶቹን መመልከት የምትችሉ መሆኑን እየገለፅን እንድትደሰቱበት እንጋብዛለን::



የዝግጅቱ ሥም፡ The Tonight Show Starring Jimmy Fallon

የአየር ላይ ቆይታ፡ 64 ዓመታት

የቀረቡ ዝግጅቶች ብዛት፡ >12,000

ስኬቶች፡

በስልጣን ላይ ያለ የአሜሪካን ፕሬዚዳንት ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበበት ዝግጅት

(ማርች 19፣ 2019)

በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በMTS Stereo የድምጽ ጥራት የቀረበ የቴሌቪዥን ዝግጅት

(እ.ኤ.አ 1984 ዓ.ም.)

የዓለማችን ረጅሙ የውይይት ትዕይንት

(Talk Show)

(እ.ኤ.አ 1954 ዓ.ም. እስከ አሁን)



TTS Official Link

ሃሽ ታግ

ከዚህ በታች የሚገኙትን ጥያቄዎች ከታች የሚገኘውን ማስፈንጠሪያ በመጫን ይመልሱ። ቀድመው የመለሱ ሶስት አንባቢዎቻችን በቀጣይ የምንሰጠው የነጻ መግቢያ ቲኬት ቅድሚያ አሸናፊ ይሆናሉ።

ጥያቄዎችን ለመመለስ እዚህ ይጫኑ

ጥያቄ 1

ባለፈው የዙር ሰላሳ እትም ላይ ቤቲ ጂ ቀርባ ነበር። አርቲስቷ በአፍሪማ ሽልማት ላይ በስንት ዘርፎች አሸንፋለች?

ጥያቄ 2

በዚህ እትማችን ሃሽ ታግ የዲጂ ፕግ ላይ ሽፋን የተሰጠው ትምህርት ቤት መጠሪያ ምን ይባላል? የስሙ ትርጉምስ ምንድነው?

ጥያቄዎችን ለመመለስ እዚህ ይጫኑ



#ፊልሞች

ተፈጣሪ

ቆይታ: 1:40
ዘውግ: ልብ አንጠልጣይ
ፀሃፊ: ኬስሮም ተክሌ
ፕሮዲዩሰር: **JE123 Studio**
ተዋንያን: ግሩም ኤርሚያስ፣ ደበበ እሸቱ፣ ሀና መርሃፅድቅ፣ ነብዩ እንድሪስ



ቁራኛዬ

ቆይታ: 1:40
ዘውግ: ታሪካዊ የፍቅር ፊልም
ፀሃፊ: ሞገስ ታፈሰ
ፕሮዲዩሰር: ሲነርጂ ሀበሻ
ተዋንያን: ዘሪሁን ሙላቱ፣ ተስፋዬ ይማም፣ የምስራች ግርማ፣ ፍሬህይወት ከልክለው፣ ፈለቀ ካሳ



ተከፍሏል

ቆይታ: 1:40
ዘውግ: አስቂኝ ድራማ
ፀሃፊ: ሳሙኤል ካሳሁን
ፕሮዲዩሰር: ሳሙኤል ካሳሁን
ተዋንያን: ሙሉአለም ጌታቸው፣ ሰለሞን ሙሄ